# እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2017 የነበረው

# የአየር ሁኔታ ግምገማ

በጁላይ የመጨረሻው አስር ቀናት በመደበኛ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ከማዳረስ አልፎ አልፎ በአንዳንዱ ቦታዎች ላይ በረዶና ነጎድጓድ እንዲሁም ከባድ ዝናብ የሚመዘገብበት ጊዜ ነው፡፡


ባሳለፍነው የጁላይ የመጨረሻው አስራ አንድ ቀናት የነበረው የዝናብ ስርጭት አብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎችን ያዳረሰ ሲሆን፤ በመጠን ረገድም ከቦታ ቦታ ይለያይ እንጂ ከቀዳሚው አስር ቀናት የተሻለ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በካቸሴ 47.2፣ በፊቼ 54.3፣ በቢሾፍቱ 49.0፣ በአቦምሳ 55.6፣ በገለምሶ 30.6፣ በጎንደር 31.8፣ በሶጊ 51.1፣ በጊዳአያና 36.5፣ በአርጆ 41.4፣ በማሻ 30.8፣ በቡኢ 33.0፣ በሊሙገነት 30.5፣ በቻግኒ 48.5፣ በአለም ከተማ 40.8፣ በኢጃጂ 35.0፣ በመተሀራ 30.8፣ በኑራኤራ 42.8፣ በሐረሪ 37.7፣ በአለማያ 47.2፣ በነጆ 69.7፣ በነቀምቴ 60.6፣ በጊንቢ 59.7፣ በባህርዳር 49.1፣ በፓዊ 56.1 እና በጋምቤላ 36.6 በሚ.ሜ. ይገኙበታል፡፡

በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አፋር፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና ከሶማሌ ክልል ጀግጅጋ እና ሲቲ ዞኖች ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የነበረው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ትግራይ፣ አማራ፣ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፣ ጋምቤላ፣ አብዛኛው ኦሮሚያ፣ ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ አፋር፣ ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና ከሶማሌ ክልል ጀግጅጋ እና ሲቲ ዞኖች ከ5-235 ሚ.ሜ. የሚደርስ ዝናብ ከ2-11 ቀናት ያህል ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2 )፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበው ዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ የአዊ እና የምዕራብ ጎጅም ዞኖች፤ ቤንሻንጉል-ጉሙዝ፤ ከጋምቤላ ክልል ዞን 2፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከኦሮሚያ ክልል ምዕራብና ምስራቅ ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ ጂማ፣ ምዕራብና ምስራቅ ሸዋ፣ የአርሲ እና የባሌ ዞኖች፤ ከአፋር ክልል ዞን 3፤ እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3)፡፡


## ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



## ካርታ 2   እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2017 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን
ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




## እ.ኤ.አ ከጁላይ 21-31/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ

## በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የጁላይ የመጨረሻ አስር ቀናት አብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አምራች አካባቢዎች የተሻለ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ ከዚህም ጋር ተያይዞ አንዳንድ ስፍራዎች ከ30.5 እስከ 69.7 በሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ ዝናብ እንዳገኙ ከተለያዩ የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች የተሰበሰቡ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህም ሁኔታ የአፈርን እርጥበት ከማሻሻል አንፃር እንዲሁም ተክሎች የሚያስፈልጋቸውን ውኃ ከማቅረብ አንጻር ገንቢ ሚና ነበረው፡፡ በተለይም የዝናቡ ወደ ሰሜን ምስራቅና ወደ ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ያደረገው መስፋፋት በባለፉት አስር ቀናት የተከሰተውን የእርትበት እጥረት በተወሰነ ደረጃ ያረገበ እና የግጦሽ ሳር እንዲሁም የመጠጥ ውኃ አቅርቦትን ያሻሻለ እንደነበረ ይታመናል፡፡ በሌላ አንፃር በአንዳንድ ሥፍራዎች ላይ የጣለዉ ከባድ ዝናብ በተለይም እርጥበት አጠር ለሆኑ፣ ዉሃን የማቆር ሥራዎችን ለመከናወን፣ ለመጠጥ ዉሃ አቅርቦት እና የግጦሽ ሣርን ለማሻሻል እንዲሁም ቁጥቋጦ ለማቆጥቆጥ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር (ካርታ 4)፡፡


ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## **እ.ኤ.አ  ከጁላይ 21-31/2017 የነበረው የአየር ሁኔታ**
## **በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ**

እ.ኤ.አ 21-31 ጁላይ 2017 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ፤ የተሻለ የእርጥበት መጠን በዋና ዋና ተፋሰሶች ላይ የላይኛውን  ክፍል ያዳረሰ መሆኑ ተስተውሏል። በመሆኑም አብዛኛው ተከዜና አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤና አዋሽ፣ የላይኛው ስምጥ ሸለቆና ዋቢሸበሌ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች ላይ የተሻለ እርጥበት የተስተዋለባቸው ናቸው። በሌላ በኩል አብዛኛው ዋቢሸበሌ፣ ገናሌዳዋ፣ የመካከለኛውና የታችኛው አፋርደናከል፣ የታችኛው አዋሽ እንዲሁም ጥቂት የታችኛው ስምጥሸለቆ ተፋሰሶች ከፊል ደረቅና ደረቅ ሁኔታ የተስተዋለባቸው ሲሆን፤ በተቀሩት የተፋሰሶች ቦታዎች ላይ ግን መጠነኛ እርጥበት ነበራቸው። በሌላ በኩል ከባድ ዝናብ የተመዘገበባቸው ተፋሰሶች ለውሃ ሀብት ግብዓት መጨመር ከፈተኛ አሰተዋፅዖ አድረጓል። በተጨማሪም በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ የነበረው ከባድ ዝናብ  ቅፅበታዊ ጎርፍና የወንዝ ሙላት አስከትሏል (ካርታ 5)።

ካርታ 5   እ.ኤ.አ ከጁላይ 21 እስከ 31/2017 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## <u>እ.ኤ.አ ከኦገስት 1-10/2017 የሚኖረው</u>
## <u>የአየር ሁኔታ አዝማሚያ</u>

በኦገስት የመጀመሪያዎቹ አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በክረምት ዝናብ ተጠቃሚ የሀገሪቱ ከፍሎች ላይ ተጠናክረው ሊቀጥሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በዚህም መሰረት በአንዳንድ የሀገሪቱ ቦታዎች ላይ ሊጠናከሩ ከሚችሉ የደመና ክምችቶች ቅጽበታዊ ጎርፍ አልፎ አልፎም በረዶ የቀላቀለ ዝናብ ሊከሰት እንደሚችል ይጠበቃል።

በዚህም መሰረት <u>ከኦሮሚያ ክልል ምሥራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ሰሜን ሸዋ፣ የአርሲና የቦሌ ዞኖች አዲስ አበባ፤ የጋምቤላ እና የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች፤ ከአማራ ክልል ምዕራብ እና ምሥራቅ ጎጃም፣ የባህር ዳር ዙሪያ፣ አዊ ዞን፣ የሰሜንና የደቡብ ጎንደር ዞኖች፤ የትግራይ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የሀድያና የጉራጌ ዞኖች፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የወላይታ፣ የሲዳማ እና የጌዲዮ ዞኖች በአብዛኛው መደበኛና ከመደበኛ በላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ ዝናብ ሊከሰት ይችላል። ከዚህም ሌላ ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ፤ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ ከአፋር ክልል ደግሞ ዞን 3 እና ዞን 5፤ ከሶማሌ ክልል የጅግጅጋ እና የሲቲ ዞኖች፣ ድሬዳዋ እና ሀረሪ በአብዛኛው ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ አልፎ አልፎም በጥቂት ሥፍራዎቻቸው ላይ ከመደበኛው በላይ ዝናብ ሊኖራቸው ይችላል። ከዚህም ሌላ የደቡብ ኦሞ እና አጎራባች የሰገን ህዝቦች ዞኖች በአብዛኛው ደረቃማ የአየር ሁኔታ እያመዘነባቸው አነስተኛ ዝናብ ሊያገኙ ይችላሉ።</u>

## <u>እ. ኤ. አ ከኦገስት 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ</u>
## <u>አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በተሰጠው የአየር ሁኔታ ትንበያ መሰረት በሚቀጥለው የኦገሰት የመጀመሪያው አስር ቀናት የመኸር ሰብል አምራች በሆኑትም ሆነ የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ አካባቢዎች የእርጥበት ሁኔታው የበለጠ እንደሚሻሻል ይጠበቃል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በትንበያው ላይ የተጠቀሱት አንዳንድ የኦሮሚያ፡ የአማራ፡ የትግራይ፡ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች፡ የጋምቤላና የቤንሻንጉል-ገሙዝ ክልሎች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ እርጥበት እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፤ ይህም ሁኔታ በተለይም ባለፉት አስር ቀናት በቂ እርጥበት ባላገኙት የትግራይ፡ የአማራ፡ የኦሮሚያና የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል አንዳንድ ዞኖች ላይ የተሻለ እርጥበት

እንደሚኖራቸው ከመጠበቁ ጋር ተያይዞ በቀጣይ ለሚያከናውኑት የግብርና እንቅስቃሴ ገንቢ ሚና እንደሚኖረው ይገመታል፡፡ በተለይም ባለፉት ጥቂት አስር ቀናት ለተዘሩና በእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙም ሆነ በተጠቀሱት አካባቢዎች ላይ ለሚገኙ ቋሚ ሰብሎች የውኃ አቅርቦት ገንቢ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ለአርብቶ አደርና ለከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለእፅዋት ልምላሜና ለመጠጥ ውኃ አቅርቦት መሻሻል አስተዋፅኦ ያበረክታል፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በትኩረት መታየት የሚገባው ነገር በተለይም የክረምቱ ዝናብ አስቀድሞ በሚወጣባቸው የሰሜንና የሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በማሳ ውስጥም ሆነ ከማሳ ውጪ ማከማቸትና ሰብሎች ለሚፈልጉት ተጨማሪ ውኃ አቅርቦት እንዲውል ከወዲሁ ዝግጅት ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህም በላይ የሚገኘው እርጥበት በተፈጥሮዓዊም ሆነ በሰው ሰራሽ መንገድ እንዳይባክን አስፈላጊውን ጥንቃቄ ማድርግ ይመከራል፡፡ በሌላ በኩል የእርጥበት እጥረት ባልታየባቸው የምዕራብና የምዕራብ አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች የሚጠበቀው የተጠናከረ እርጥበት በተለይም ገና በዝቅተኛ እድገት ደረጃ ላይ በሚገኙ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም በዝቅተኛ ቦታዎች ላይ በሚገኙ የእርሻ ማሳዎች ላይ የጎርፍ አደጋ እንዳይከሰት መፋሰሻዎችን ከወዲሁ ማዘጋጀትም ሆነ ነባር መፋሰሻዎች አለመደፈናቸውን የማረጋገጥ ተግባራት ከወዲሁ ማየትና ክትትል ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ይሆናል፡፡

## እ. ኤ. አ ከኦገስት 1-10/2017 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃዉ ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

የክረምቱ ዝናብ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ውስጥ በመጠንና በስርጭት ረገድ በተጠናከረ ሁኔታ የክረምት ዝናብ በሚያገኙት ተፋሰሶች ላይ ቀጣይነት እንዳለው ትንበያው ያመለክታል። ይህንን ተከትሎ በአብዛኛው ተከዜ፣ አባይ፣ ባሮአኮቦ፣ ኦሞጊቤ፣ የላይኛውና መካከለኛው አዋሽና ስምጥሸለቆ፣ የላይኛው ገናሌዳዋና ዋቢሸበሌ እንዲሁም ጥቂት የላይኛው አፋርደናከል ተፋሰሶች መደበኛና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ እንደሚያገኙ የሚጠበቅ ሲሆን፣ የታችኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆና ባሮአኮቦ እንዲሁም የመካከለኛው ዋቢሸበሌ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ዝናብ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። በተለይ የዝናብ ስርጭታቸው ከመደበኛው በላይ የሚጠበቅባቸውና በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ደግሞ ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው አካባቢዎች የወንዞች ሙላት እንዲሁም የጎርፍና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ስለሚችል ከወዲሁ ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል።